

☙56-1❧

# ”ለትግል የሚዳርጉን ሁኔታዎች”
# (Challenges)
# የሰውን የሕይወት አቅጣጫ ይለውጣሉ

አንድ ጊዜ በታሪክ ጸሀፊነቱ ዝናን ያተረፈው ቻርለስ ቢርድ፥ “የተለያዩ የዓለም ሁኔታዎችንና ታሪኮችን ስትመረምር፣ በሕይወትህ የተማርከው ከፍተኛ ትምህርት ምንድነው?” የሚል ጥያቄ ቀረበለት። ለተጠየቀው ጥያቄ ወዲያው የሰጠው መልስ፥ “ጨለማ ሲሆን፥ ያኔ ከዋክብቶች ብቅ ይላሉ” የሚል ነበር። መልሱ ከጥያቄው ጋር የማይሄድ ይምሰል እንጂ፥ ፍሬ ያለው አባባል ነው። የሌላውን ሰው የሕይወት ታሪክ አጥንቶ ሳይሆን፥ በግል ሕይወቱ ተላማምዶት ያገኘው ከፍተኛ መገለጥ ይመስላል። ሰው በህይወቱ ትክክለኛ አቅጣጫ መያዙና እያደገ መሆኑ የሚታየው፥ በአታጋይ ሁኔታ” ውስጥ ሲያልፍ ነው። ያጋጠመው ሁኔታ “አታጋይ” ወይንም ጨለማ ቢመስልም፥ የሕይወቱ ውበት ጎልቶ እንዲታይ ምክንያት ይሆነዋል። አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ልጅ ከትንሽ እህቱ ጋር ሆኖ ተራራ ሲወጣ፥ እህቱ በጣም ደከማትና በመበሳጨት “እዚህ ተራራ ላይ የተመቻቸ መንገድ የሌለው ለምንድነው? አባጣ ጎርባጣና ኮረኮንች የበዛበት ብቻ ለምን ሆነ?” ስትል ጠየቀቻው። ወንድምየውም ሲመልስላት፥ “አባጣ ጎርባጣ የሆነው አቀበቱን ለመውጣት እንድትችዪ የእግር መርገጫ እንዲሆንልሽ ነው” አላት። በሕይወታችን አባጣ ጎርባጣ ወይንም “ለትግል የሚዳርገን ሁኔት” ሲያጋጥመን፥ “እንቅፋት አጋጠመኝ” ብለን በማማረር ፈንታ፥ ወደሚቀጥለው የሕይወት ደረጃ የምንሸጋገርበት የእግራችን መርገጫ እንደሆነ አድርገን ብንቀበለው፥ “ክፉ ነው’ ከምንለው ነገር በጎ ነበር ማግኘት እንችላለን።

“ለትግል የምዳርጉን ሁኔታዎች” ሲያጋጥሙን ሚዛናችንን ስተን እንዳንወድቅ ራሳችንን አስቀድመን ማዘጋጀት ይገባናል (2ኛ ጢሞ. 2፥21)። “የሕይወትን ማዕበል” መለማመድ የምንችለው፥ ጥሩ የዓየር ሁኔታ ባለበት ወቅት ራሳችንን ያዘጋጀን እንደሆነ ነው (2ጢሞ. 2፥3)። አንዴ ማዕበሉ መንቀሳቀስ ከጀመረ በኋላ እግራችንን የምናሳርፍበት ቦት አናገኝም። በትግላችን አሸናፊ ለመሆን ሁልጊዜ በቅድሚያ መዘጋጀትና መለማመድ ይረዳናል። አንድ የስኮትላድ ተወላጅ የሆነ ክርስቲያን በሞት አልጋ ለይ ሆኖ ሲያጣጥር አጠገቡ ሆና ታስታምመው የነበረችው ልጁ የአባቷን ሁኔት ተመልክታ፥ “አባባ! አንድ ምዕራፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላንብብልህ?” ስትል ጠየቀቻው። አባትየውም “ይቅር አታንብቢልኝ! ማዕበሉ እየመጣ ነው! ቢሆንም ዓይሩ ጥሩ በነበረበት ወቅት አስቀድሜ ቤቴን ሠርቻለሁና ምንም አልፈራም” አላት። የሕይወት ማዕበል ሲያጥለቀልቀን፥ ታገልን ከማዕበሉ በላይ ሆነን መንሳፈፍ እንድንችል፥ ለሚያገጥመን “አታጋይ ሁኔታ (Challenge) አስቀድመን እራሳችንን እናለማምድ። ለመሆኑ “ለትግል የሚይዳርጉን ሁኔታዎች” ምንድናቸው? ብዙ አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች የተለያየ ገለጻና አስተያየት ሰጥተውበታል። “በርኪ” የተባለው ጸሀፊ “...አታጋይ ሁኔታ፥ ጥሩ አስተማሪያችን ሲሆን፥ ተዘጋጅቶ የተሰጠንም እኛ ራሳችንን ከምናወቀው የበለጠ ከሚያውቀንና እንዲሁም እኛ ራሳችንን ከምንወደው የበለጠ ከሚወደን ነው። “ትግላችን” የበለጠ ችሎታችንን የሚቅርጽ፣ ድፍረታችንን የሚጨምር ነው። በዚህ ዓይነት “ጎጂያችን ነው” የምንለው ረዳታችን ሆኖ ይገኛል። “ከአታጋይ ሁኔታ” ጋር የምናደርገው ግብ ግብ፥ ዓላማችን አጥርተን እንድናውቅ የሚያደርገን ከመሆኑም በላይ፥ በሁሉም አቅጣጫ እንድንመለከት ይረዳናል። “እንደ ነገሩ” ወይንም “ለብ ለብ” ያልን እንድንሆን አይተወንም” አለ።

“ለትግል የሚዳርጉን ሁኔታዎችን” በሚመለከት ሀሳብ ላይ ሦስት የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉ እንመለከታለን።

1ኛ. ሰው በተፈጥሮ ታግሎ ሲያሸንፍ ደስ የሚለው ክፍል ነው። “አታጋይ ሁኔታ” (Challenge) ለእድገቱ ምክንያት ይሆናል ብሎ ስለሚያምንና ስለሚገምት አታጋይ ሁኔታ ሲያጋጥመው እንደ ትልቅ ዕድል ይቆጥረዋል (ያዕቆብ 1፥2-4)። የሚያታግል ሁኔታም ካላገኘ ሁኔታዎቹን ራሱ ሆን ብሎ የሚፈጥርበት ጊዜ አለ። በሕይወቱ “አታጋይ ሁኔታዎችን” (Challenge) የማይሸሽ ሰው ፥ በማንኛውም አቅጣጫ ውሳኔ

ለመስጠት ድፍረት ይኖረዋል።

2ኛ. “ለትግል የሚዳርጉትን ሁኔታዎች” የሚፈራውና የሚሸሸው ክፍል ነው። በተፈጥሮው ቀስ ብሎ የሚራመድ፣ “አዲስ ነው” ነው ብሎ ከሚያስበው ሁኔታ ጋር ራሱን በቀላሉ ማለማመድ የማይሆንለት በመሆኑ፥ አስቸጋሪና አታጋይ ነው ብሎ ከሚያስበው ሁኔታ ሁሉ ራሱን በተቻለው መጠን ለማሸሽ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ይታያል። በዚህ ምክንያት ውሳኔ መወሰን በጣም ይፈራል።

3ኛ. በነዚህ በሁለቱ መካከል የሚገኝ ሌላ ክፍል አለ፤ ይኸውም ታግሎ ማሸነፍ የሚችል መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን ብቻ “ለትግል የሚዳርጉትን ሁኔታዎች” ለመቀበል ፈቃደኛ የሚሆነው ነው። በዚህ ምክንያት ውሳኔ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ችግር እንደማይፈጥርበት ሲያውቅና እርግጠኛ ሲሆን ብቻ ነው። ብዙዎቻችን በዚህኛው ክፍል ውስጥ እንገኛለን።

ሰው በሕይወቱ ወደ አዲስ የዕድገት ምዕራፍ መድረስ የሚችለው “ትግል” ባለበት ሁኔታ ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኛ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው (1 ጴጥ. 1፥6-7)። “ትግል ያለበት ሕይወት” ደግሞ ከአደጋ ሁልጊዜ ነጻ ላይሆን ይችላል። “አስጊነት” ከሌለበት ግን፥ ትግሉ እውነተኛ መሆኑ ያጠራጥራል። አንድ ጸሐፊ “ሊጠቅመኝ የመጣ መሆኑን መጨረሻ ላይ ሳልረዳው ያለፈ አንድም ዓይነት “ትግል” በሕይወቴ አጋጥሞኝ አላውቅም። በሞት አልጋ ላይ ሆነው ሞታቸውን ከሚጠባበቁት ክርስቲያኖች መካከል፥ በምድር ላይ ሕይወቱን በመከራና በትግል በማሳልፉ ምክንያት ያጉረመረመና ያማረረ አንድም ክርስቲያን አላጋጠመኝም” ያለው እውነት ነው። ፕሉታርክ የተባለው ጸሀፊ ደግሞ “ብልጽግና ሰውን ብዙ ንብረት ያስጨብጣል፣ ነፍስን ያሳብጣል፣ ሰውን ከሆነው በላይ ብርቱና ኀያል እንደሆነ አድርጎ ያሳያል። ሌሎችን ደግሞ በንቀት ዓይን ወደ ታች እንዲመለከት ያደርጋል። የጨዋ ጠባይ ያለው ሰው ግን በትግል ውስጥ ያለፈ ነው፤ ሕይወቱም በኀይል የሚያበራና ጎልቶ የሚታይ ነው” ሲል ተናግሯል።

ብዙዎቻችን አደጋን ስለምንፈራ “አታጋይ” ከሆነ ሁኔታ ሁሉ በተቻለን መጠን ሸሽተን ለመኖር ከፍተኛ ጥረት እንደርጋለን። “አደጋ የለበትም” ብለን ከምንለው ክልል ውስጥ ከሆንን ደግሞ፥ በምንምን ዓይነት ከዚያ ክልል ውጪ መውጣት አንፈልግም። ሌላው ችግራችን በትግል ተሸንፎ መታየት በሌሎች ዘንድ የሚያስንቀን መስሎ ስለሚሰማን፥ አሸናፊዎች መሆናችንን እርግጠኞች ካልሆንን በቀር ምንም ዓይነት አዲስ ነገር በድፍረት አንሞክርም። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ እግዚአብሔር የሕይወታችንን አቅጣጫ ለመለወጥ “ለትግል የሚዳርጉን ሁኔታዎች” ውስጥ እንድናልፍ ሲያደርግ ጸንተን መቆም ይገባናል (1ጢሞ. 6፥12)። “ትግል” ለመሆኑ ምን ማለት ነው? የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል። ዌብስተር “ትግልን” ሲገልጸው “ከፍጻሜ ለመድረስ ቆራጥነትና ሙሉ ልብነትን የሚጠይቅ ነገር ሁሉ “ትግል” ነው ይለዋል። ይህን የዌብስተርን ገለጻ የምቀበል ከሆነ፥ የብዙዎቻችን ሕይወት “አታጋይ” በሆነ ሁኔታ (Challenge) የተሞላ እንደሆነ እናያለን። ጥዋት ከዕንቅልፋችን ተነስተን ወደ ዕለት ተግባራችን ስንሄድ፥ ይሄ ራሱ ለብዙዎቻችን “ትግል” ነው። ስለዚህ ለአንዱ “ትግል” የሆነበት ለሌላው ላይሆን ይችላል።

**የሰው ዕለታዊ ተግባር “ለትግል የሚዳርገው ሁኔታ” መሆን ይችላል።**

በየቀኑ የምንሠራው ተመሳሳይነት ያለው የዕለት ሥራችን፣ ራሱን የቻለ “ትግል” ሊሆን ይችላል። በቀን ስምንት፣ አንዳንዱም ከዚያ በላይ የሆነ ሰዓት ተደጋጋሚ በሆነ ሥራ ላይ በመሠማራት ሳምንቱን፣ ወሩንና ዓመቱን ያሳልፋል። ጥዋት ልክ ከእንቅልፉ ሲነቃ መጀመሪያ ወደ አዕምሮው የመመጣው፣ ያ የሚሰለች ሥራ፣ ያ የማይወደው የሥራ ቦታ፣ ያ ነዝናዛ የሥራ አለቃው ነው። ምርጫ ስለሌለው ቢወድም ባይወድም በግድ ለመኖር ሲል ብቻ ተነስቶ ወደ ሥራው ይሄዳል። እንዲሁም የቤት እመቤቷ ቤተሰቧን ለመመገብ፣ ለቤቷ ውበት ለመስጠት፣ ልጆቿንና ባሏን ደስ ለማሰኘት ስትል ከጥዋት እስከ ማታ የምትሠራውን ሥራ ይህን ያህል ባትወደው፣ ሥራው መሥራት ስላለበትና የራሷን የሥራ ድርሻ ለመወጣት ብቻ ሳትታክት ጎንበስ ቀና ስትል ትውላለች። ይህንን ተደጋጋሚና “አሰልቺ ተግባር” ተቀብለን መኖር የሚያስችለን አንደኛው ምክንያት፣ በተመሳሳይ ሕይወት ውስጥ የምኖረው እኛ ብቻ አለመሆናችንን መረዳት ስንችል ነው። ሀዋርያው ጳውሎስ “…በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብሆን መርካትን ተምሬአለሁ” (ፊልጵ. 4፥11) እንዳለው፥ እኛም ማንኛውንም ዓይነት የኑሮ ሁኔታ ተቀበለን ደስ ብሎን ለመኖር ራሳችንን ማለማመድ ይኖርብናል (መክብብ 3፥22)። አንዳንድ ሰው ግን በየዕለቱ የሚሠራው ሥራ አንድ ዓይነት ቢሆንም አይሰለቸውም፥ እንዲያውም ቀኑን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚያሳልፈው አስቀድሞ ስለሚያውቅ፥ ዕቅድ ማውጣትና እንዲሁም ሁኔታዎችን ቅደም ተከተል ማስያዝ ስለሚችል ደስ ይለዋል። ስለዚህ ለእንዲህ ዓይነቱ ሰው ይሄ በረከት እንጂ “አታጋይ” ሁኔታ አይደለም። “አታጋይ” ለሚሆንባቸው ሰዎች ግን፥ የዕለት ተግባራቸው ምንም ያህል አሰልቺ ቢሆንም፥ ሁኔታውን እንዳለ ተቀበለው ለመኖር ራሳቸውን ማለማመድና እንዲሁም ለዕድገት ፈቃደኞች መሆን ይገባቸዋል።

ሰው የሚያጋጥመው አዲስ ነገር፥ “ለትግል” የሚዳርገው ሁኔታ” ሊሆንበት ይችላል።

ሰው በሕይወቱ ያላየው አዲስ ነገር ሲያጋጥመው፥ “ከዚህ በፊት እንደማውቀውና እንደተለማመድኩት ዓይነት አደጋ የሌለበት ይሆን?” ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ብዙ ጊዜ ከዚህ በፊት ያልተለማመደው አዲስ ነገር መሆኑን ሲያውቅ፤ ማሰብና መስጋት ይጀምራል። ወደ ኋላም ለማፈግፈግ ይቃጣዋል። ይሁን እንጂ ካፈገፈገ ማደግ እንደማይችል ማደግ ካልቻለ ደግሞ እንደሚሞት ያውቃል። ስለዚህ “አታጋይ የሆኑትን ሁኔታዎች” ለመቀበል ራሱን ያዘጋጃል። ከዚህ በፊት በሕይወታቸው ያልተለማመዱት አዲስ ነገር ሲያጋጥማቸው፥ በአዲስ የሕይወት ጎዳና ለመራመድ ፈቃደኞች ከሆኑ፥ ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት መካከል ትምህርት እንዲሆነን ነህምያን፣ ኢዮብንና ሙሴን እንመለከታለን።

ሀ. ነህምያ የእስራኤልን የፈረስ ቅጥር ለመገንባት ሲነሳ፥ ከዚህ በፊት ተመሳሳይ የሆነ የመገንባት ልምምድ ስላልነበረው ለሁኔታው ፍጹም እንግዳ ነበር። የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለምሥራት የተነሳው የኢየሩሳሌም መፈራረስና እንዳልነበረች መሆን ልቡን ስለበላው ብቻ ነበር። በራዕዩ ተባባሪ እንዲሆኑት ሕዝቡን ለመቀስቀስ ያደረገውን ጥረት ሲገልጽ፥ “…እንግዲህ ያለውን ችግር ሁሉ ተመልከቱት፣ ምክንያቱም ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ሆናለች፤ የቅጽር በሮችዋም በእሳት ወድመዋል፤ ስለዚህ ተነስተን የከተማይቱን ቅጽሮች እንሥራ፤ የደረሰብንንም ሀፍረት እናስወግድ! አልኳቸው። ቀጠል አድርጌም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር መሆኑና እንዴትም እንደረዳኝ፥ ንጉሥ ነገሥቱም የነገረኝን ሁሉ ገለጥሁላቸው” ይላል (ነህምያ 2፥17)። ነህምያ ከአቅሙ በላይ ከሆነ፥ በቀላሉ ሊወጣው ከማይችለው ሁኔታ ጋር ለመግጠም ወስኖ ተነሳ። የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ መሥራት ለነህምያ “አታጋይ ሁኔታ” ያለበት ነበር። በልቡ ውስጥ እንደ እሳት የሚነደው “የመቆጨት ስሜት” በሥራ ተተርጉሞ ለማየት፥ በቅድሚያ የተነሳበት ዓላማ ከፍተኛ ዋጋ ቢያስከፍለውም፥ ያንን ለመክፈል ዝግጁ መሆን ነበረበት። ኅላፊነቱን ተቀብሎ ግንባታውን እንደ ጀመረ፥ ልዩ ልዩ ዕንቅፋቶች አጋጥመውታል (ነህምያ 6) ያጋጠሙትን እነዚያን ዕንቅፋቶች መወጣት ያስቻለው፥ ሥራው ፍጻሜ አግኝቶ ለማየት የነበረው ውሳኔና ጉጉት ነበር። ነህምያ ምኞቱን በተግባር ላይ በሚያውልበት ወቅት ያጋጠሙት ልዩ ልዩ “አታጋይ ሁኔታዎች” ምን እንደነበሩ የበለጠ ለማየት፥ የነህምያን መጽሐፍ በሙሉ ማንበብ ይጠቅማል። እኔና እናንተ ሀሳባችንን በሥራ ለመተርጎም ስንነሳ የሚደርስብንን ዓይነት ትግል በነህምያም ላይ ደርሶበታል። በሰው ኃይልና ጉልበት ሊታለፉ የማይችሉ ልዩ ልዩ ዕንቅፋቶችና ትግሎች አጋጥመውታል። በትግሉ አሸናፊ እንዲሆን የረዱት ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው፥ ዓይኑን በእግዚአብሔር ላይ ማድርጉ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ ልቡን በማጽናት የግንባታ ሥራውን በትጋት መሥራቱ ብቻ ነበር። የተነሳበት ዓላማ ስላወቀ ተቃዋሚ ኃይልም ቢነሳበት፥ ዓላማውን ሳይለቅ በቆራጥነት ሠርቶ መጨረስ ቻለ።

.....................................................................................

በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።